መካነ ሕይወት አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን

Mekane Hiwot Abune Gebre Menfes Kidus Ethiopian Orthodox Tewahedo Church


ጥር ፳፯ ቀን ፳፻፪ ዓም
Feb. 04 2010

# በአትላንታ የመካነ ሕይወት አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ቅዳሴ ቤት ተባርኮ አገልግሎት መስጠት ጀመረ፡፡

በአትላንታ የመካነ ሕይወት አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ጥር ፲፭ ቀን ፳፻፪ (January 23 2010) በብጹዕ አቡነ አብርሃም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የዋሽንግተን እና አካባቢው ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ እና የቅዱስ ሲኖዶስ አባል ቅዳሴ ቤቱ ተባርኮ አገልግሎት መስጠት ጀመረ፡፡ በእለቱም ብጹዕ አቡነ ማርቆስ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የስብከተ ወንጌል የበላይ ሀላፊ እና የቅዱስ ሲኖዶስ አባል በእንግድነት ተገኝተዋል፡፡ እንዲሁም በአካባቢው በሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት የሚያገለግሉ ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን ከሌሊቱ 4፡00 am ጀምሮ ተገኝተው በእሉን በተመለከተ ስብሐተ እግዚአብሔር አድርሰዋል፡፡

የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ መላከ ሕይወት ቀሲስ ዕርገተ ቃል በስፍራው በእሉን ለማክበር የተገኙትን ሊቃነ ጳጳሳት፣ካህናት ፣ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን እና ምእመናን የእንኳን ደኅና መጣችሁ መልዕክት ካስተላለፉ በኋላ ብጹዕ አቡነ አብርሃም ከዛሬ 3 ሺህ አመት በፊት ጠቢቡ ሶሎሞን የእግዚአብሔርን ቤት በሠራ ጊዜ እግዚአብሔር ቤተ መቅደሱን እንደባረከና በውስጡ በንጽህና ሆኖ የሚቀርበውን ፀሎትና ልመና እንደሚቀበል እንደገለፀለት ሁሉ ዛሬም በዚህ ቤተመቅደስ የሚጸለየውን ፀሎት እንደሚሰማ ለዚህም ምእመናን በአንድ ልብ ሆነው በፍቅር እና በሰላም አምልኮተ እግዚአብሔርን መፈጸም እንዳለባቸው ሰፋ ያለ አባታዊ ትምህርትና ቃለ ቡራኬ ሰጥተዋል፡፡

በማያያዝም ብጹዕ አቡነ ማርቆስ ‹‹ከእናንተ ልጁ ዳቦ ቢለምነው ድንጋይ የሚሰጠው ማነው›› በሚል ርዕስ እግዚአብሔር ኃጢያታችንን ሳይመለከት ልመናችንን ሰምቶ በቤቱ ተገኝተን ምስጋና እንድናቀርብ እንደፈቀደ ሁሉ የምንሻውን አውቆ እንደሚሰጠንና ለዚህም ራሳችንን በቤተ መቅደሱ ውስጥ ዝቅ በማድረግ በትህትና እርሱን ልንማጸን እነደሚገባን መንፈሳዊ መልእክት አስተላልፈው የእለቱ ክብረ በዓል በፀሎት ተጠናቋል፡፡

ወስብሐት ለእግዚአብሔር




4540 Memorial Drive, Suite A
Decatur, GA 30032

Atl.abo.eotc@gmail.com

P.O.Box: 831233
Stone Mountain, GA 30083